# የኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ክፍያ (EIP): የማነቃቂያ ቼክ

CASH CAMPAIGN OF MARYLAND
Creating Assets, Savings and Hope

DHHS MONTGOMERY COUNTY
Department of Health and Human Services

## ምንድን ነው?

የኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ ክፍያ (EIP) የማነቃቂያ ቼክ እየተባለም ይጠራል። ይህ በመንግስት የሚከፈል የአንድ ጊዜ ክፍያ ሲሆን በ COVID-19 ምክንያት የተከሰተ የኑሮ ጫናን ለማቃለል የሚሰጥ ነው።

| <u>ለግለሰብ</u> | <u>በጋራ</u> |
|---|---|
| $1, 200 | $2,400 |
| ✷ ዕድሜው ከ17 ዓመት በታች ለሆነ እያንዳንዱ ልጅ $500 ይሰጣል | |

## እርስዎ ብቁ ነዎት?

የአሜሪካ ዜጋ፣ ቋሚ ነዋሪ ወይም የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟሉ የውጭ ሃገር ዜጋ ከሆኑ ብቁ ነዎት:

- ✓ የጸና የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ካለዎት
- ✓ የሌላ ግብር ከፋይ ጥገኛ አለመሆንዎት ከተረጋገጠ
- ✓ የተስተካከለ አጠቃላይ ገቢዎ በተወሰነ መጠን ስር የሚወድቅ ከሆነ

## የማመለከተው እንዴት ነው? ግብርዎን ያሳውቁ

አንዳንድ ሰዎች ክፍያቸውን ወዲያውኑ ያገኛሉ:

- ለ2018 ወይም 2019 የፌዴራል ገቢ ግብራቸውን ያሳወቁ ግለሰቦች

<u>እንዲሁም፣ የሚከተሉትን ክፍያዎች የሚያገኙ ሰዎች:</u>

- የማህበራዊ ዋስትና ጡረታ
- የአካል ጉዳተኝነት ጥቅማ ጥቅም (SSDI)
- የጥቃት ሰለባዎች ጥቅማ ጥቅሞች
- ተጨማሪ የማህበራዊ ዋስትና ገቢ (SSI) ተቀባዮች
- የቀድሞ ጦር አባላት ጉዳዮች ጥቅማ ጥቅም ካሳ እና
- የጡረታ (C&P) ጥቅማ ጥቅም ተቀባዮች
- የባቡር መንገድ የጡረታ (RRB) ጥቅማ ጥቅሞች

## ግብር የማሳያውቁ ሰዎች

✷ ገቢያቸው ዝቅተኛ የሆነ ወይም ምንም ገቢ የሌላቸውና የግብር ተመላሽ ያላቀረቡ ሰዎች ክፍያውን ለማግኘት ብቁ ናቸው። ወደ IRSwebsite በመግባት ግብር የማያሳውቅ ሰው ቅጽ መሙላት አለባቸው።

<u>ግብር የማያሳውቅ ሰው ቅጽ ላይ የሚያስፈልግ መረጃ:</u>

- ሙሉ ስም፣ ወቅታዊ የመልእክት መቀበያ አድራሻና የኢሜይል አድራሻ
- የትልውልደ ቀንና የጸና የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር
- የባንክ ሒሳብ ቁጥር፣ የሒሳቡ ዓይነትና ራውቲንግ ቁጥር (ካለ)
- በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ ከ IRS የተሰጠዎት ማንነትን መጠበቂያ የግል መታወቂያ ቁጥር (IP PIN) ካለ
- የመንጃ ፈቃድ ወይም በግዛት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ ካለዎት
- በ2019 መስፈርቱን ለሚያሟላ ለእያንዳንዱ ልጅ: ስም፣ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ወይም የጉዲፈቻ የግብር ከፈያ መለያ ቁጥር እና ከእርስዎ ወይም ከባለቤትዎ ጋር ያለው ዝምድና

## ቀነ ገደቦች

### <u>ግብር ማሳወቂያ</u>

ጁላይ 15

✷ግብርዎን እስከ ጁላይ 15 ድረስ ለማሳወቅ ካልቻሉ የጊዜ ማራዘሚያ ለማግኘት ማመልከት አለብዎ።

✷ጁላይ 15 ለ IRS የሚገባ ግብር የሚከፈልበት የመጨረሻ ቀን ነው።

✷ከጁላይ 15 በኋላ፣ ለ IRS መከፈል የሚገባው ክፍያ ቅጣት እየወለደ ይሄዳል።

### <u>የማራዘሚያ ቀን</u>

አክቶበር 15

✷ ይህ ግብር ለማሳወቅ የሚፈቀድ የጊዜ ማራዘሚያ ነው።

✷ይህ ለ IRS መከፈል ያለበትን ግብር ለመክፈል የሚሰጥ የጊዜ ማራዘሚያ **<u>አይደለም</u>** ።

✷ይህ የማነቃቂያ ቼክ ለማግኘት መረጃዎን የሚያቀርቡበት የመጨረሻ ቀን ነው።

# የክፍያ መረጃ

✸ ክፍያዎትን ማግኘት የሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ።

| | |
|---|---|
| ቀጥተኛ ተቀማጭ | ቀጥተኛ ተቀማጭ ገንዘብዎን በፍጥነት ለማግኘት የሚችሉበት ዘዴ ነው። ክፍያው እርስዎ በግብር ተመላሽ ወይም ግብር በማያሳውቅ ሰው ቅጽ ላይ ወደሞሉት የባንክ ሒሳብዎ ገቢ ይደረጋል። |
| በፖስታ | የባንክ ሒሳብ መረጃዎን ካላሳወቁ፣ ክፍያዎ በፖስታ ቤት በኩል ይላክልዎታል።<br><br>ክፍያው በቼክ ወይም በቅድመ ክፍያ ዴቢት ካርድ ወጪ ይደረጋል። |

# የቅድመ ክፍያ ዴቢት ካርድ

✸ የቅድመ ክፍያ ዴቢት ካርድ ተመላሽ አድራሻ ባለው ኤንቨሎፕ የሚላክ ሲሆን፣ ላኪውም ***Money Network Cardholder Services***ነው።

✸ ቪዛ ካርድ በሚቀበሉ ቦታዎች ሁሉ የቅድመ ክፍያ ካርድዎን መጠቀም ይችላሉ።

✸ የቅድመ ክፍያ ካርድዎን በመጠቀም ጥሬ ገንዘብ ማግኘት ይችላሉ። እባክዎ የክፍያዎችን ዝርዝር ለማየት eipcard.com ይጎብኙ።

✸ ካርድዎን ስራ ለማስጀመር ወደ 1.800.240.8100 መደወል አለብዎት።

✸ ካርዱን ስራ ለማስጀመር የሚያስፈልግ መረጃ:

- የካርድ ቁጥር
- የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎ የመጨረሻዎቹ 6 ዲጂቶች
- ከካርድዎ በስተጀርባ ላይ የተጻፈ ባለ 3 ዲጂት የሴኪዩሪቲ ኮድ

**ለተጨማሪ መረጃ፣ ይህን ይጎብኙ፡ irs.gov**

MC311 ANSWERING TO YOU

Helping People. Changing Lives. community Action PARTNERSHIP MONTGOMERY COUNTY, MARYLAND COMMUNITY ACTION AGENCY

ልዩ ትብብር ለመጠየቅ፡ እባክዎትን 240-777-1123 ይደውሉ ወይም ኢሜይል VITA@montgomerycountymd.gov. ቲቲዋይ ተጠቃሚዎች፡ ሜሪላንድ ሪሌይ 711 ይደውሉ